የታክስ ሒሳብ መዝገብ አያያዝ





1.1ትርጓሜ

"ሰነድ" ማለት

- ማኝኛውም የግብይት መከናወንን፣ ስለግብይቱ ምንነት፣ስለ ግብይት አከናወኞች የሚያስረዳ ወይም የሚያረጋግጥ፤

ሀ) የሂሳብ መዝገብ፣ ሪከርድ፣የሒሳብ መዝገብ መግለጫ፣ የመመዝገቢያ ሰነድ፣ የባንክ መግለጫ፣ ደረሰኝ፣ ቫውቸር፣ ውል ወይም ስምምነት፣ የጉምሩክ ዲክላራሲዮን፤

ለ) ፈቃድ በተሰጠው አካል ወይም የታክስ ወኪል የተሰጠ የምስክር ወረቀት ወይም መግለጫ፤ ወይም

ሐ) በኤሌክትሮኒክ የመረጃ ማከማቻ መሳሪያ ውስጥ የተከማቸ /የተያዘ/ ማንኛውም መረጃ ወይም ዳታ የሚያካትት፤ ማለት ነው።

ሀ"የታክስ ሒሳብ መዝገብ" ማለት ሁሉንም የፋይናንስ ግብይቶችና በንዑስ ምድቦች ውስጥ የተከፋፈሉ ሁሉንም የገንዘብ ልውውጦች የሚይዝ ሆኖ፣ታክስ ከፋዩ የንግድ ሥራ ሀብትና ዕዳ እንዲሁም የዕለት ተዕለት ገቢውን እና ወጪውን የሚመዘግብበት መዝገብ (journal and ledger) ነው።

ለ"የታክስ ሒሳብ መዝገብ መግለጫ" ማለት የታክስ ከፋዩ የንግድ እንቅስቃሴ ያለበትን ደረጃ የሚያሳይ ሰነድ ሲሆን የሀብትና ዕዳ መግለጫ፣ የገቢና ወጪ መግለጫ፣ የገንዘብ ፍሰት እንቅስቃሴ መግለጫ፣ የአንጡራ ሀብት (capital) ለውጥ መግለጫ፣ የተጠራቀመ ትርፍ ወይም ኪሳራ መግለጫ፣የትርፍና ኪሣራ መግለጫ፣ የምርት ሂደት መግለጫ እና የምርት ወጪ መግለጫን የሚያካትት ነው።

ሐ) ጊዜያዊ የታክስ ሂሳብ መዝገብ፡-

ማንኛውም ግብር ከፋይ የድርጅቱን ግዥ እና ሽያጭ የሚመዘግብበት ሊኖረዉ የሚገባ የሂሳብ መዝገብ ነዉ።

1.2. IFRS እና የታክስ ሂሳብ መዝገብ

➢እንደሚታወቀዉ አገራችን በአዋጅ ቁጥር 847/2014 እ.ኤ.አ የአለምአቀፍ የፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀትና አቀራረብ ደረጃ /International Financial Reporting Standards/ ወይም IFRS የተቀበለች አገር ናት።

ሆኖም ከዚህ አዋጅ በፊት እና እስከ አሁንም (በተለይም የቅ/ጽ/ቤታችን ግብር ከፋዮች) ጭምር ወደ ስርዓቱ በመግባት ላይ ያሉ እንጅ በሙሉነት ያልተከናወነ እና ለዚሁም ባለቤት የሆነዉ የመንግስት ተቋም የኢትዮጵያ ሂሳብ አያያዝና ኦዲት ቦርድ የሚከታተለዉ ጉዳይ ነዉ። ስለሆነም IFRS በሙያዊ እይታ ሲታይ አለማቀፋዊ የሂሳብ አያያዝና ሪፖርቲንግ ስለሆነ ለጠቅላላ/General Purpose/ የሚዘጋጅ እንጅ ለታክስ ፤ለአባደሪዎች፤ ለባለቤቶች ለባለድርሻ አካላት ተብሎ የተለየ አይደለም ይህንኑ ሪፖርትን የአጠቃቀም ደረጃና ቅደም ተከተል ግን ሊለያይ ይችላል።

የሪፖርት ማቅረቢያ ጊዜ ከ 2015 ዓ.ም/ እ.ኤ.አ 2023/ ሙሉ ደረጃዎችን /full IFRS/ የሚተገብሩ፡

- ዓመታዊ ሽያጭ፡- 300 ሚሊዮን ብር እና ከዚያ በላይ፣
- ጠቅላላ ሀብት/ንብረት፡- 200 ሚሊዮን ብር እና ከዚያ በላይ፣
- ጠቅላላ ዕዳ፡- 200 ሚሊዮን ብር እና ከዚያ በላይ፣ እንዲሁም
- የሠራተኛ ቁጥር ፡- 200 እና ከዚያ በላይ ያላቸው ሆኖ ከአራቱ መስፈርቶች ሁለቱን የሚያሟሉ

አነስተኛ እና መካከለኛ ድርጅቶች(SMEs)

- ዓመታዊ ገቢ/ሽያጭ፡- ከ50ሚሊዮን ብር እስከ 300ሚሊዮን ብር፣
- ጠቅላላ ሀብት/ንብረት፡- ከ50 ሚሊዮን ብር እስከ 200 ሚሊዮን ብር፣
- ጠቅላላ ዕዳ፡– ከ50 ሚሊዮን ብር እስከ 200 ሚሊዮን ብር እና

የሠራተኛ ቁጥር፡- ከ50-200 ሠራተኛ ያላቸው ሆኖ ከአራቱ ሁለቱን መስፈርቶች የሚያሟሉ ለአነስተኛ እና መካከለኛ ድርጀቶች የሚያገለግለ ዉን /IFRS for SMEs/ ይከተላሉ።

ክፍል-2-

የታክስ ሂሳብ መዝገብ አያያዝና የሂሳብ መግለጫ ይዘት፤



2.1. የሂሳብ መዝገብ አያያዝ ለግብር/ታክስ ዓላማ

አዲስ በተሻሻለው አዋጁ አንቀፅ 86 መሠረት፡

ሀ) **የደረጃ "ሀ" ግብር ከፋይ** በገቢ ግብር ህግና በዚህ መመሪያ መሰረት፣

ለ) **የደረጃ "ለ" ግብር ከፋዮች** የሂሳብ መዝገብ መያዝ ይችላሉ። የያዙት የሂሳብ መዝገብ ተቀባይነት ካገኘ የሚከፍሉት ግብር የሚወሰነው በሂሳብ መዝገባቸው እና በዚህ አዋጅ ሰንጠረዥ "ሐ" መሰረት ይሆናል"

የሂሳብ መዝገብ አያያዝ ለግብር/ታክስ ዓላማ የቀጠለ----

➢የግብር ከፋዮች የግብር ከፋይ ደረጃ እንደተጠበቀ ሆኖ፦ በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979/2008 አንቀፅ-10 ጀምሮ የተመላከቱት ሰንጠረዦች (ከሰንጠረዥ "ሀ" እስከ ሰንጠረዥ "ሠ" እንደየገቢ አይነቶቹ በተናጠል የሂሳብ መዝገብ መያዝ ይኖርበታል።

- በሠንጠረዥ ‘ሐ’ መሠረት ግብር የመክፈል ግዴታ ያለበት እና ከአንድ በላይ የንግድ ሥራ መስክ ገቢ የሚያገኝ የደረጃ “ሀ” ግብር ከፋይ፣ለእያንዳንዱ የተለየ የሥራ መስክ የሂሳብ መዝገቦችን እና ደጋፊ መረጃዎችን በተናጠል መያዝ አለበት።”

የሂሳብ መዝገብ አያያዝ ለግብር/ታክስ ዓለማ የቀጠለ--------

ሐ) የካፒታል ሀብት በማስተላለፍ በሚገኝ ጥቅም ላይ ግብር ይከፈልበታል የተባለውን ሀብት የሚያስተላልፍ ሰው፣ የሚተላለፈውን ሀብት በተመለከተ፤የሒሳብ መዝገብ መያዝ አለበት ።

የካታል ሀብት በማስተላለፍ የሚገኝ ጥቅም ማለት በተሻሻለው በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 1395/2017 አንቀጽ - የ61 ካፒታል ሀብትን በማስተላለፍ የሚገኝ ጥቅም (የማይንቀሳቀሱ ሀብቶች) እና (ቦንድና አክሲዮኖች) ግብር ላይ ተፈጻሚ የሚሆነው መጣኔ 15% (አስራ አምስት በመቶ) ይሆናል።

የሂሳብ መዝገብ አያያዝ ለግብር/ታክስ ዓላማ

- ግብር የሚከፈልበትን ሃብት በማስተላለፍ የሚገኝ ጥቅም ነው የሚባለው በሚከተለው ቀመር ተሰልቶ የሚገኘው ጥቅም ነው፦
- ሐ - (ሀ + ሀ*ለ) = ግብር የሚከፈልበት ጥቅም
- ለዚህ ቀመር አፈጻጸም፦
- ሀ - ሀብቱ የተፈራበት/የተገዛበት ዋጋ
- ለ - የዋጋ ንረት ማስተካከያ 30% (ሠላሳ በመቶ)
- ሐ - ሀብቱ የተላለፈበት ዋጋ

የካፒታል ሀብት በማስተላለፍ ለሚገኝ ጥቅም የሚያዝ የሂሳብ መዝገብ

የካፒታል ሀብት በማስተላለፍ ከሚገኝ ጥቅም ታክስ የመክፈል ግዴታ ያለበት ማንኛውም ግብር ከፋይ፤

ሀ) የተላለፈው የካፒታል ሀብት የተገኘበትን ዋጋና ቀን፣

ለ) ሀብቱን ለማሻሻል የወጣን ወጪ ጨምሮ ሌላ ማንኛውም ለሀብቱ የወጣ ወጪ እና

ሐ) ሀብቱ በሚተላለፍበት ጊዜ ለግብር ከፋዩ የተከፈለ የማስተላለፊያ ዋጋ አጠቃሎ የሚይዝ የሂሳብ መዝገብ መያዝ አለበት።

የካፒታል ሀብት በማስተላለፍ....

2/ የካፒታል ሀብትን በማስተላለፍ የሚገኝ ጥቀም" ማለት የካፒታል ሀብትን በሽያጭ፣ በስጦታ (በእርዳታ) ፣ በዓይነት መዋጮ ወይም በድርሻ መልክ ማስተላለፍ ማለት ነው።

3/ የካፒታል ሀብት በአይነት መዋጮነት ለተጠቃሚ ሲተላለፍ

ሀ/የተላለፈው የካፒታል ሀብት ማስተላለፊያ ዋጋ ወይም

ለ/የማስተላለፊያው ዋጋው ባልታወቀ ጊዜ ሀብቱ በተላለፈበት ወቅት የነበረው የገበያ ዋጋ የካፕታል ድርሻው ዋጋ ተደርጎ ይቆጠራል።

የካፒታል ሀብት በማስተላለፍ....

ምሳሌ1፦ ተስፋ የሚባል አንድ ድርጅት የንግድ ህንጻ ግንኙነት ለሌለዉ ግብር ከፋይ ሸጠ

Sale of Capital Asset (Building with Gain)

ሀ. የንግድ የህንጻው የሽያጭ ዋጋ 13,050,000.00

ለ. የንግድ ህንጻዉ የተገዛበት ዋጋ 8,500,000.00

ህንጻዉ የተገዛበት ጊዜ ሐምሌ 1/2009 ዓ.ም

ህንጻዉ የተሸጠበት ሰኔ 30/2017 ዓ.ም

ሐ. Accumulated Depreciation 3,400,000.00

መ. የህንጻዉ የመዝገብ ዋጋ 5,100,000.00

የካፒታል ሀብት በማስተላለፍ....

1. የዋጋ ንረት ማስተካከያ ስንት ነው

2. የተገኘ ጠቅላላ ጥቅም ስንት ነው

3.የካፒታል ዋጋ ጥቅም ግብር ስንት ነው

4. ለንግድ ሥራ ገቢ ግብር ስንት ነው

የካፒታል ሀብት በማስተላለፍ....

1. የዋጋ ንረት ማስተካከያ

= የንግድ ህንጻዉ የተገዛበት ዋጋ 8,500,000.00* የዋጋ ንረት ማስተካከያ 30% = 2,550,000

2. የተገኘ ጠቅላላ ጥቅም

=የተሸጠበት ዋጋ - (የህንጻዉ የመዝገብ ዋጋ + የዋጋ ግሽበት ማስተካከያ)

= 13,050,000 - (5,100,000 +2,550,000)= 5,400,000 Total gain

3. የካፒታል ዋጋ ጥቅም ግብር

=(የተሸጠበት ዋጋ (Sale) – (የመጀመሪያ ዋጋ ብር (OC) + የዋጋ ግሽበት ማስተካከያ))*15%

= (13,050,000 - (8,500,000+2,550,000)) = 2,000,000*15% = 300,000

4. ለንግድ ሥራ ገቢ ግብር

=(ህንፃ የተገዛበት ዋጋ – የተጣራ መዝገብ ዋጋው)*30% = (8,500,000-5,100,000) = 3,400,000 *30 % = 1,020,000.00

2.4.ግብር ከፋይ መያዝ ያለበት የሰነድ ዓይነት(አን-7-)

- **የተጨማሪ እሴት ታክስ የሚከፈልባቸዉ፤ ከተጨማሪ እሴት ታክስ ነጻ እና በዜሮ-ሬት ያላቸዉን አቅርቦቶች እና ሽያጭ ዋጋ ዝርዝር እና በተጨማሪ እሴት ታክስ ማስታወቂያ እና ከዓመታዊ ገቢ ማስታወቂያ መካከል ላለ ልዩነት የተሰራ የማስታረቂያ የሂሳብ ሪፖርት መቅረብ ይኖርበታል።**
- **የተለያዩ ፕሮጀክቶች የተከናወኑ ከሆነ በእያንዳንዱ ፕሮጀክት የወጣ ገቢ እና ወጭ፤**
- **የታክስ ሂሳብ መዝገብ ትክክለኛነትን ለማረጋገጥ ሌላ አስፈላጊ ሰነድ መቅረብ ይኖርበታል።**

ግብር ከፋይ መያዝ ያለበት...

- በውል መሠረት ለሚፈፀም ሥራ የውል (የውል ማሻሻያ) ሰነድ፣ የክፍያ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት፣ የልኬት ማስረጃ (bill of quantity) ፣ እና ሌላ በሶስተኛ ወገን ሊረጋገጥ የሚችል የሶስተኛ ወገን ማስረጃ ካለ፤
- ክፍያ የፈፀመው ባንክ ክፍያ ለመፈጸም ማረጋገጫ የሰጠበት የባንክ ፈቃድ፣
- ለድርጅት ግብር ከፋዮች በሚመለከተው አካል የፀደቀና የተመዘገበ የካፒታል መጠን የሚገልጽ ሰነድ፣ የድርጅቱ የመመስረቻ ጽሁፍ እና ሌሎች በንግድ ህግ መሰረት የሚዘጋጁ ሰነዶች፤
- ከደንበኛ እና አቅራቢ የሚሰጥ ሕጋዊ የግብይት ደረሰኝ ወይም ታክስ የተከፈለበት ሕጋዊ ሰነድ፣እንዲሁም የታተሙ ደረሰኞችን ከእነ ህትመት ፈቃዳቸው፣የጥሬ ገንዘብ ወይም የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ ውጤቶች(ጆርናል፣ዜድ ሪፖርትና የመሳሰሉት)፤

ግብር ከፋይ መያዝ ያለበት ሰነድ...

- የሠንጠረዥ “ሀ” ግብር ከፋይ ለተቀጣሪዎቹ በየወሩ ደመወዝ የከፈለበትንና ተቀናሽ ያደረገውን ታክስ፣ የጡረታ መዋጮ እና ሌሎች ተቀናሾችን የሚያሳይ የደመወዝ መክፈያ መዝገብ (payroll) ፣
- የንግድ ሥራ ሀብት ትክክለኛ ዋጋ ያልተገኘለት እንደሆነ የንግድ ሰራ ሀብት ዋጋ የመገመት ሥልጣን ከተሰጠው አካል የተዘጋጀ ትክክለኛ የዋጋ መግለጫ ሰነድ፣
- በታክስ ዘመኑ የተወገደ የንግድ ሥራ ሀብት የሽያጭ ዋጋ፣ በተፈጥሮ አደጋ ለወደመ ወይም በሌላ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ለውጥ ለተደረገበት ሀብት የተፈፀመ የካሣ ክፍያ ካለ የክፍያ ማስረጃ፤

ግብር ከፋይ መያዝ ያለበት...

- **የታክስ እፎይታ ወይም የታክስ ነፃ መብት** ያለው ግብር ከፋይ ይህንኑ የሚያረጋግጥ ማስረጃ፤
- የታክስ ስሌት የተዘጋጀው በተፈቀደላቸው የሒሳብ ባለሙያዎች ወይም በውጭ ኦዲተሮች ከሆነ በሚመለከተው አካል ለሂሳብ ባለሙያዎች ወይም ለውጭ ኦዲተሮች የተሰጠውን የታደሰ የምዝገባ የምስክር ወረቀት፤
- ታክስ ከፋዩ ታክስ ያስታወቀበት የታክስ ማስታወቂያ ሰነድ እና ታክስ የከፈለበት ሰነድ፤

2.5.ግብር ከፋይ የሚይዘው የታክስ ሒሳብ መዝገብ

1/ የደረጃ ''ሀ'' ግብር ከፋይ የሒሳብ መዝገቡን የሚይዘው በፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀትና አቀራረብ አዋጅ መሠረት መሆን አለበት።

2/ ከላይ የተገለጸው ድንጋጌ ቢኖርም የኢትዮጵያ የሂሳብ አያያዝና ኦዲት ቦርድ ያወጣው አስገዳጅ የትግበራ ጊዜ እስከሚደርስ ወይም እስከሚጠናቀቅ ድረስ አጠቃላይ ተቀባይነት ያለውን የሒሳብ አያያዝ መርህ (Generally Acceped Accounting Principles) መሠረት በማድረግ ግብር ከፋዩ የሂሳብ መዝገቡን ማዘጋጀት አለበት።

አንቀጽ 50:- የደረጃ “ለ” ግብር ከፋዮች ግብር አከፋፈል

- ንዑስ አንቀጽ (1)፡- በዚህ አዋጅ በሌሎች አንቀጾች ወይም በሌላ የታክስ ህግ የተደነገገው ቢኖርም የደረጃ “ለ” ግብር ከፋዮች ግብር የሚከፍሉት በጠቅላላ ገቢያቸው ላይ ይሆናል።
- ንዑስ አንቀጽ (2)፡- ግብሩ የሚጣለው እና የሚከፈለው በግብር ዓመቱ ውስጥ ከዕቃ እና ከአገልግሎት ሽያጭ በሰበሰቡት ጠቅላላ የሽያጭ ገቢ ላይ ነው።
- ንዑስ አንቀጽ (3)፡- በዚህ አንቀጽ መሰረት የሚከፈለው ግብር ማስከፈያ መጣኔ የሚከተለው ይሆናል፦

አንቀጽ 50:- የደረጃ “ለ” ግብር ከፋዮች ግብር አከፋፈል

ግብር የሚከፈልበት አመታዊ ጠቅላላ ገቢ	መጣኔ (በመቶኛ)
0 — 100,000	2%
100,001 — 500,000	3%
500,001 — 1,000,000	5%
1,000,001 — 1,500,000	7%
1,500,001 — 2,000,000	9%

አንቀጽ 50:- የደረጃ “ለ” ግብር ከፋዮች ግብር አከፋፈል

- ንዑስ አንቀጽ (4)፡- የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ ለሚከተሉት ተፈጻሚ አይሆንም፦
- ሀ) የሚከተሉትን ጨምሮ የሙያ አገልግሎት ለሚሰጡ ሰዎች፡-
- ለሂሳብ አያያዝ ሙያ፤
- ለአርኪቴክቶች፤
- ለአማካሪዎች፤
- ለግንባታ ስራ ተቋራጮች፤
- ለመሃንዲሶች፤
- ለፋይናንስ፣ ለኢኮኖሚ እና ኢንቨስትመንት ባለሙያዎች፤
- ለጤና ባለሙያዎች፤
- ለህግ ባለሙያዎች፤
- ለ) ለተጨማሪ እሴት ታክስ ለተመዘገቡ ታክስ ከፋዮች፤ እና
- ሐ) የሂሳብ መዝገብ በማቅረብ በሠንጠረዥ “ሐ” መሰረት በተጣራ ታክስ የሚከፈልበት ገቢ ላይ ግብር ለመክፈል ለመረጡ የደረጃ “ለ” ግብር ከፋዮች፤

አንቀጽ 50:- የደረጃ “ለ” ግብር ከፋዮች ግብር አከፋፈል

- **ንዑስ አንቀጽ (5)፡-** በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ 4 በተዘረዘሩት ሙያዎች የተሰማሩ ግብር ከፋዮች በዚህ አዋጅ ለደረጃ “ሀ” የሚጠየቀውን የሂሳብ መዝገብ የመያዝ ግዴታ አለባቸው።
- **ንዑስ አንቀጽ (6)፡-** የደረጃ “ለ” ግብር ከፋዮች በእያንዳንዱ የግብር ዓመት የንግድ ሥራ ገቢ ግብር የሚከፍሉት የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ በሚወሰነው የግብር አከፋፈል ዘዴ ነው።

2.6.የንግድ ዕቃ ቆጠራ (Stock Inventory) (አን-9-)

- የታክስ ሂሳብ መዝገብ የሚይዝ ማናቸውም ግብር ከፋይ፦
- ✓የንግድ ዕቃዎችን በነጠላ አመዘጋገብ በንብረት መመዝገቢያ መዝገብ ሊመዘግብ ይገባል።
- ✓ከላይ የተገለጸው ቢኖርም የንግድ ዕቃዎችን በነጠላ አመዘጋገብ መመዝገብ ካልተቻለ ለታክስ ባለስልጣኑ አስቀድሞ በማሳወቅ የንግድ ዕቃዎች ብዛት እና ዋጋ እየተገለጸ የጥቅል (በእሽግ፣ በደርዘን፣ በኩንታል ወይም በሌሎች ሙያዊ ተቀባይነት ባላቸው መለኪያዎች) አመዘጋገብን በመጠቀም በወጥነት ሊመዘግብ ይገባል።
- ✓የንግድ ዕቃው ሲመዘገብ በጥቅም ላይ የዋለ መለኪያን መቀየር በሚያስፈልግበት ጊዜ መቀየር ያስፈለገበትን ምክንያትና የተደረገውን ማስተካከያ ማስተካከያው በተደረገ 30 ቀናት ውስጥ ለታክስ ባለስልጣኑ ማሳወቅ ይኖርበታል።
- ✓የንግድ ዕቃዎችን በቆጠራ ጊዜ የመዘገበበት ስም እና ዕቃዎችን ሲሸጥ የሚመዘግብበት ስም አንድ አይነት መሆን አለበት።

2.7. የንግድ ሥራ ሀብት መዝገብ

➢ግብር ከፋዩ ያለውን የንግድ ሥራ ሀብት እንደ ዓይነቱ እና እንደ አገልግሎቱ በመለየት የሚመዘግብበት የንግድ ሥራ ሀብት መዝገብ ሊኖረው የሚገባ ሲሆን የዚህ ዓይነት መዝገብ፣

✓ እያንዳንዱ የንግድ ሥራ ሀብት የተገዛበት ወይም የተገኘበት ቀን እና ዋጋ፣

✓ በግብር ዘመኑ የንግድ ሥራ ሀብቱን ለማሻሻል የተደረገ ማንኛውም ከተጣራ የመዝገብ ዋጋ ከሀያ በመቶ በላይ ወይም በታች የሆነ ወጪ፣

✓ በዓመቱ መጨረሻ የንግድ ሥራ ሀብቱ ያለውን የተጣራ የመዝገብ ዋጋ ፣

✓ የእያንዳንዱ የተጠራቀመ የእርጅና ቅናሽ መጠን የሚያሳይ ስሌት የያዘ መሆን አለበት።

➢ኢንቨስትመንት የሚያካሂድ ግብር ከፋይ የኢንቨስትመንት ሥራው ተጠናቆ የኢንቨስትመንቱ አጠቃላይ ካፒታል እስኪታወቅ ድረስ በየጊዜው የሚወጣው ወጪ የሚመዘገብበት ራሱን የቻለ መዝገብ (ledger) ሊኖረው ይገባል።

የዕዳ እና የተከፋይ ሂሳቦች መዝገብ (book of liability)

1/ ማንኛውም ግብር ከፋይ ብድር በሚወስድበት ጊዜ ወይም የዱቤ ግዥ በሚፈጽምበት ጊዜ ለዱቤ ግብይቱ በሚሰጠው ደረሰኝ ላይ የሚገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ የዕዳ መመዝገቢያ መዝገብ መያዝ ያለበት ሲሆን መዝገቡ፤

ሀ) የብድር ወይም የዱቤ ሽያጭ ስምምነትን፣

ለ) የዕዳ አከፋፈል ሁኔታን (Mode of payment) ፣

ሐ) የአበዳሪው ወይም ዕቃ ወይም አገልግሎት በዱቤ የሸጠው ሰው ሙሉ መረጃን፣

መ) የተመዘገበ የዕዳ መያዣን (ዋስትናን) ካለ አካቶ የያዘ መሆን አለበት።

- ማንኛውም ግብር ከፋይ ዕቃን ወይም አገልግሎትን በዱቤ በመሸጥ የሚያገኘው ወለድ በሰንጠረዥ “ሐ” መሰረት ግብር የሚከፈልበት ይሆናል።

የታክስ ሒሳብ መግለጫ

➢ግብር ከፋዩ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን የሒሳብ መግለጫዎች ማዘጋጀት እና ለታክስ ባለስልጣኑ ማቅረብ አለበት።

- ✓የሀብት እና የዕዳ መግለጫ (balance sheet)፣
- ✓የጥሬ ገንዘብ ፍሰት ወይም ገቢና ወጪ መግለጫ (Cash flow statement)፣
- ✓የድርጅቱ የካፒታል ለውጥ መግለጫ (Change of capital statement)፣
- ✓የትርፍና ኪሣራ መግለጫ (Profit and loss statement)፣
- ✓አምራች ድርጅት ከሆነ የምርት ሂደት መግለጫ (Production statement) እና
- ✓ለተመረተ ምርት የወጣ የምርት ወጪ መግለጫ (Statement of Cost of Goods Manufactured)፣

የታክስ ሒሳብ መግለጫ...

- ታክስ ከፋዩ ንግድ ፈቃድ ያወጣበት የንግድ መስክ ከአንድ በላይ በሆነ ጊዜ ንዑስ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር (Sub-TIN) ተጠቅሞ እያንዳንዱን የንግድ እንቅስቃሴ በተናጠል በተዘጋጀ የሂሳብ መዝገብ በመመዝገብ በዓመቱ መጨረሻ በዋናው የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር የተጠቃለለ የሒሳብ መግለጫ (aggregated financial statement) ማዘጋጀት አለበት።
- ከአንድ በላይ በሆኑ ክልሎች ወይም የከተማ አስተዳደሮች ቤት በማከራየት ወይም ሌላ የንግድ ሥራ በማከናወን የተሰማራ ግለሰብ ግብር ከፋይ ለእያንዳንዱ ክልል ወይም ከተማ አስተዳደር በተናጠል የተዘጋጀ የሒሳብ መግለጫ ማቅረብ አለበት።

ጥቃቅን እና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ስለሚይዙት የታክስ ሂሳብ መዝገብ

1/ ጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች እንደ ግለሰብ ታክስ ከፋይ ተቆጥረው ዓመታዊ ገቢያቸውን መሠረት በማድረግ በሚመደቡበት የግብር ደረጃ መሠረት የታክስ ሒሳብ መዝገብ እንዲይዙ ይደረጋል።

2/ አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የደረጃ "ሀ" ግብር ከፋይ ስለሆኑ የደረጃ "ሀ" ግብር ከፋይ መያዝ ያለበትን የታክስ ሂሳብ መዝገብ ሊይዙ ይገባል።

ሰነድን በሚመለከተው አካል ስለማስመዝገብ

➢ከዚህ በታች የተዘረዘሩ ውሎች ወይም የውል ስምምነቶቹ ከ3 ወር በላይ የሚቆዩ ከሆነ በተፈረሙበት ጊዜ በሚመለከተው አካል መመዝገብ አለባቸው።

- ✓ለንግድ ዓላማ የሚውል የቤት ኪራይ፤
- ✓የመጋዘን ኪራይ፤
- ✓የጥናት አገልግሎት ግዢ፣
- ✓ማንኛውም አይነት የማሽነሪ ኪራይ፣
- ✓የንግድ ተሸከርካሪ ኪራይ፣
- ✓የኪራይ ውሉ የተደረገው ከመንግስት መስሪያ ቤቶች ጋር ከሆነ ውሉ መመዝገብ አያስፈልገውም።

ሰነድን በሚመለከተው አካል ስለማስመዝገብ...

- የተጠቀሱትን አገልግሎቶች ለማግኘት የሚደረገው ስምምነት የተገለጹትን አገልግሎቶች ለመስጠት የንግድ ፈቃድ ካለው ሰው ጋር የተደረገ እንደሆነ እና አገልግሎት ሰጪው የሂሳብ መዝገብ የመያዝ ግዴታ ያለበት ከሆነ ውሉ መመዝገብ ሳያስፈልገው ለአገልግሎት ሽያጭ የሚቀርበው ህጋዊ ደረሰኝ እና ለአገልግሎቱ የተደረገው ክፊያ በባንክ ተፈጽሞ ከቀረበ በቂ ይሆናል።
- በሚመለከተው አካል ያልተመዘገበ የውል ሰነድ በማስረጃነት በሚቀርብበት ጊዜ በቴምብር ቀረጥ ህግ መሰረት ሁለት እጥፍ የቴምብር ቀረጥ የተከፈለበት መሆን አለበት።

የታክስ ሒሳብ መዝገብ ሰነድ ስለማዘጋጀት

➢የታክስ ሂሳብ መዝገብ መያዝ ያለበት ግብር ከፋይ፡-

✓የታክስ ሂሳብ መዝገቡ የሙያ ፈቃድ ባለው የሂሳብ ወይም የታክስ አዲት ባለሙያ እና/ወይም ማህበር ወይም በሂሳብ አያያዝ የትምህርት ዝግጅት ባለው ተቀጣሪ የሂሳብ ሰራተኛ እንዲዘጋጅ ሊያደርግ ይችላል።

✓ግለሰብ ሆኖ አስፈላጊውን የሂሳብ አያያዝ የትምህርት ዝግጅት እና ልምድ ያለው ከሆነ የታክስ ሂሳብ መዝገቡን ራሱ ሊያዘጋጅ ይችላል።

✓ድርጅት ከሆነ ሥራ አስኪያጅ ወይም ሰራተኛ አስፈላጊውን የሂሳብ አያያዝ ትምህርት ዝግጅት ያለው ከሆነ የታክስ ሂሳብ መዝገቡን ሊያዘጋጅ ይችላል።

✓ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም የታክስ ሂሳብ መዝገቡን ያዘጋጀው ሰው የሂሳብ አያያዝ ትምህርት የተመረቀ ስለመሆኑ ከተዘጋጀው የሂሳብ መዝገብ ጋር አያይዞ ማረጋገጫ ማቅረብ አለበት።

በታክስ ሒሳብ መግለጫ ላይ ስለሚደረግ ማስተካከያ

- ግብር ከፋዩ የሚያቀርበው የታክስ ሒሳብ መዝገብ መሰረታዊ ጉድለት ካልተገኘበትና ለታክስ አወሳሰን የሚያስፈልጉ መረጃዎችን ያልያዘ መሆኑ ካልተረጋገጠ በስተቀር ውድቅ አይደረግም።
- ግብር ከፋዩ ያቀረበው የታክስ ሂሳብ መዝገብ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ጉድለቶች የተገኙበት እንደሆነ መዝገቡን ውድቅ ማድረግ ሳያስፈልግ ጉድለቶቹ እንዲስተካከሉ ተደርጎ ግብሩ በመዝገቡ መሰረት ይወሰናል።

በታክስ ሒሳብ መግለጫ ላይ ስለሚደረግ ማስተካከያ--

- ✓ በታክስ ሒሳብ መግለጫው ላይ በሙሉ ወይም በከፊል ያልተገለፀ ገቢ መኖሩ ሲረጋገጥ፤
- ✓ በደረሰኝ ላይ የተሰበሰበው ገቢ ድምር በታክስ ሒሳብ መግለጫ ላይ ከሰፈረው ገቢ ጋር ሲነፃፀር ልዩነት ያለው መሆኑ ሲረጋገጥ፤
- ✓ ግብር ከፋዩ ያስታወቀው የንግድ ሥራ ገቢ ከታክስ ነፃ የተደረገውን ግብይት ሳይጨምር ለተጨማሪ ዕሴት ታክስ ካስታወቀው ዓመታዊ ገቢ ጋር ሲነፃፀር ልዩነት የተገኘበት ሲሆን፤
- ✓ በታክስ ከፋዩ የታክስ ሒሳብ መግለጫ ላይ የተገለፀው ያልተሸጠ ዕቃ ዋጋ በቆጠራ ከተገኘው የዕቃ ዋጋ ጋር ሲነፃፀር ልዩነት ያለው ሆኖ ሲገኝ፤

በታክስ ሒሳብ መግለጫ ላይ ስለሚደረግ ማስተካከያ--

- ✓ ግብር ከፋዩ ባቀረበው **ያልተመዘገበ ውል** ላይ የተገለፀ የንግድ ቤት እና የመጋዘን ኪራይ፣ የኮንስትራክሽን ማሽን ኪራይ፣ የንግድ ተሸከርካሪ ኪራይ ወይም የረጅም ጊዜ ጥናት አገልግሎት ወጪ ሲገኝ፣
- ✓ በደረሰኝ አስተዳደር መመሪያ መሠረት **ተቀባይነት በሌለው ደረሰኝ ተገልጾ የቀረበ ወጪ ሲቀርብ፤**
- ✓ **በአዋጁ ያልተፈቀደ ወጪ ተይዞ ሲገኝ፤**

በታክስ ሒሳብ መግለጫ ላይ ስለሚደረግ ማስተካከያ--

- ✓ ግብር ከፋዩ በገቢነት ያልገገለጸው ሆኖ በግብር ከፋዩ ባንክ ሂሳብ ገቢ የተደረገ ገንዘብ፣ከንግድ ስራ ያልተገኘ ወይም ግብር የሚከፈልበት ጊዜ ስለመሆኑ በተገቢው ህጋዊ ማስረጃ በግብር ከፋዩ ተረጋግጦ መቅረብ አለበት::
- ✓ በባንክ ሂሳብ ገቢ የተደረገው ገንዘብ የንግድ ስራ ገቢ ስላለመሆኑ በግብር ከፋዩ ካልተረጋገጠ በታክስ ህግ መሰረት ግብር ይወሰንበታል።

ግብር ከፋዩ ያቀረበው የታክስ ሒሳብ መግለጫ ተቀባይነት የሚያጣበት ሁኔታ

- ያቀረበውን የሒሳብ መግለጫ ትክክለኛነት በራሱ ወይም የሂሳብ መግለጫውን ያዘጋጀው ባለሙያ በታክስ ባለስልጣኑ ሲጠየቅ በተገቢው ማስረጃ በማቅረብ ያላረጋገጠ እንደሆነ፣
- የሒሳብ መዝገብ እና ለግብር አወሳሰን አስፈላጊ የሆኑ ደጋፊ ሰነዶችን እንዲያቀርብ በጽሁፍ ተጠይቆ ያላቀረበ እንደሆነ፣
- በደረሰኝ አስተዳደር መመሪያ መሠረት በባለሥልጣኑ ያልተፈቀደ ደረሰኝ ተጠቅሞ የተዘጋጀ የሒሳብ መዝገብ ካቀረበ፤
- በፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀት ደረጃዎች መሰረት የተዘጋጀ የሂሳብ መግለጫ ማቅረብ ሲገባው ካላቀረበ የቀረበው የሂሳብ መግለጫ ውድቅ ይደረጋል።
- ያቀረበው የሂሳብ መግለጫ ውድቅ ከተደረገበት መዝገብ ባለመያዝ የሚጣለው ቅጣት ተፈፃሚ አይሆንበትም።

ምሳሌ2፡-

- ጫምባላላ የተባለ በአስመጭነት ንግድ ስራ የተሰማራ ድርጅት የ2016 በጀት ዓመት ሂሳብ መግለጫ ለተመዘገቡበት ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤት መስከረም 20 ቀን 2017 ዓ.ም አሳዉቀዋል፡- ያሳወቁት የትርፍና ኪሳራ መግለጫ በዋናነት ሲታይ፡-

ግብር ከፋዩ ለ2016 በጀት ዓመት ያሳወቁት የትርፍና ኪሳራ መግለጫ

Sales			21,000,000.00
	Beginning Inv.	5,700,000.00	
	Purchases	18,000,000.00	
	Available For Sale	23,700,000.00	
	Ending Inventory	7,000,000.00	
Cost of Goods Sold			16,700,000.00
Gross Profit			4,300,000.00
Gen.& Adm Expense			850,000.00
Net Profit			3,450,000.00
Profit Tax			1,035,000.00
Net Profit After tax			2,415,000.00

የሂሳብ ማስተካከያ

ሆኖም የግብር ከፋዩ የሂሳብ መግለጫ በገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቱ በሚታይበት ወቅት፤የሚከተሉት ማስተካከያዎች ነበሩበት፡-

ሀ) ከዚህ ቀደም በእጅ በእጅ የተ.እ.ታ ደረሰኝ ቁጥር Fs No. 0000198 ቀን መጋቢት 5/2016 ዓ.ም ለተፈጸመ ሽያጭ ብር 350,000.00 (ከተ.እ.ታ በፊት) ሂሳብ መግለጫዉ ላይ አልተካተተም፤

ለ) በ2016 በጀት ዓመት በቆጠራ የተረጋገጠ የእቃ ዋጋ ብር 7 ሚሊዮን ብር ሳይሆን 6 ሚሊዮን 8 መቶ ሃምሳ ሽ ብር ብቻ መሆኑ በመረጋገጡ፤

ሐ) ግብር ከፋዩ በአስተዳደራዊ ወጭነት ለበጀት ዓመቱ ያሳወቁት ብር 850,000.00 ሲሆን ህጋዉ ደረሰኝ የቀረበለት ግን ብር 750,000.00 ብቻ መሆኑ ፤

የሚሉት ግኝቶች ብቻ በገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቱ የተረጋገጠ ቢሆንና ከዚህ ወጭ ሌላ ተጨማሪ ክፍተት የሌለዉ ሂሳብ መግለጫ ነዉ ያሳወቁት ብለን ብናስብ፡- ግብር ከፋዩ ያሳወቁት ሂሳብ መግለጫ ዉድቅ ሳይደረግ እነዚህ ማስተካከያዎች በማድርግ ሂሳቡን ስሩ?።

ማስተካከያ የተደረገበት ለ**2016** በጀት ዓመት የቀረበ የትርፍ እና ኪሳራ መግለጫ

Sales			21,350,000.00
	Begining Inv.	5,700,000.00	
	Purchases	18,000,000.00	
	Avilable For Slae	23,700,000.00	
	Ending Inventory	6,850,000.00	
Cost of Goods Sold			16,850,000.00
Gross Profit			4,500,000.00
Gen.& Adm Expense			750,000.00
Net Profit			3,750,000.00
Profit Tax			1,125,000.00
Net Profit After tax			2,625,000.00

የወጪ ማስረጃ ውድቅ ሲደረግ ተቀናሽ ስለሚደረግ ወጪ

- የሂሳብ መዝገብ የሚይዝ ማንኛውም ግብር ከፋይ ያቀረበው የወጪ ማስረጃ በታክስ ባለስልጣኑ ተቀባይነት ባለማግኘቱ ውድቅ ሲደረግ፣ ወጪው ገቢውን ለማመንጨት ወይም የድርጅቱን እንቅስቃሴ ለማስቀጠል ወይም ለድርጅቱ ዋስትና ለመስጠት የወጣ ወጪ መሆኑ ተረጋግጦ፤
- ✓ ለቋሚ የንግድ ሥራ ሀብት ዕቃው በተሰራበት ወይም በተገዛበት ወቅት የዕቃው የገበያ ዋጋ 70% ፣
- ✓ ለሌላ ዕቃ ወይም አገልግሎት ግዥ ሲሆን ዕቃው ወይም አገልግሎቱ ሲገዛ ወይም ሲሰጥ የነበረው የገበያ ዋጋ 65% በወጪነት በመያዝ ተቀናሽ ይደረጋል።
- ✓ ተቀባይነት ያጣው ወጪ ገቢውን ለማመንጨት ወይም የድርጂቱን እንቅስቃሴ ለመስቀጠል ወይም ለድርጂቱ ዋስትና ለመስጠት የወጣዉ ወጪ አለመሆኑን ከተረጋገጠ ወጪዉ ሙሉ በሙሉ ዉድቅ ይደረጋል።
- ✓ ከላይ የተገለጸው 70% እና 65% ወጪ ግብይት ሳይኖር ለሚሰጥ ደረሰኝ ወይም ለህገ-ወጥ ደረሰኝ ተፈጻሚነት የለዉም።

ማጣቀሻ (Referance)

- የገቢ ግብር አዋጅ ቁ. 979/2008
- የተሻሻለው የገቢ ግብር አዋጅ ቁ. 1395/2017
- የታክስ አስተዳደር አዋጅ 983/2008
- የገቢ ግብር ደንብ ቁ. 410/2009
- የታክስ አስተዳደር ደንብ ቁ. 410/2009
- *መመሪያ ቁ. 138/2010 ታክስ በግምት ስለሚወሰንበት ሁኔታ የወጣ መመሪያ*
- *መመሪያ ቁ. 176/2014 የሂሳብ መዝገብ አያያዝ መመሪያ*
- *መመሪያ ቁ. 1/2011 ከገቢ ግብር ነፃ የተደረጉ ገቢዎች አፈፃጸም መመሪያ (የገንዘብ ሚኒስቴር)*
- *መመሪያ ቁ. 5/2011 ስለ ተቀናሽ ወጪዎች የወጣ መመሪያ (የገንዘብ ሚኒስቴር)*
- *መመሪያ ቁ. 8/2011 የካፒታል ሀብቶችን በማስተላለፍ በሚገኝ ጥቅም ላይ ስለሚከፈል ግብር አፈፃፀም (ገንዘብ ሚኒስቴር)*
- *መመሪያ ቁጥር 146/2011 የንግድ ስራ ከተቋረጠ በኋላ በተገኘ ገቢ ላይ ግብር ስለሚከፈልበት ሁኔታ ለመወሰን የወጣ መመሪያ*

አመሰግናለሁ !!!

